# መለስ የኢትዮጵያዊያን ባለውለታ ናቸው፤ ህዝቡም ለህዳሴው በመትጋት ውለታውን ይከፍላል፤

ታሪኩ 8/28/12

ኢትዮጵያዊያን በምድራቸው የሆነውንም ሆነ የሚሆነውን ሁሉ ጠንቅቀው የሚያጤኑ አርቆ አሳቢ ሕዝቦች ናቸው፡፡ እኒህ ጥንታዊ ህዝቦች ለማወደስም ሆነ ለመኮነን አይጣደፉም፡፡ እያንዳንዷን ክስተት ግን በዝምታም ቢሆን በአእምሯቸው ይከትባሉ፡፡ ሁኔታዎችን በአንክሮ እየመረመሩ ያወጣሉ ያወርዳሉ፡፡ የሚበጃቸውንና  የሚጎዳቸውንም በአግባቡ ያጤናሉ፡፡

የጥንት የዓለም ታሪክ ባለቤት የሆኑት እነዚህ ህዝቦች ጀግና ናቸው፡፡ በአገርና ወገን ጥቅም ላይ የሚመጣን ማንኛውንም አደጋ ይጋፈጣሉ፡፡ ህይወትን ጭምር በመክፈል መስዋእት ይሆናሉ፡፡ ኢትዮጵያዊያን ከሁሉም በላይ ለእውነትና ፍትህ እውን መሆን ዘውትር ይታገላሉ፡፡ እውነት ስትረገጥ፤ ፍትህ ስትዛባ በዝምታ አያልፉም፡፡ ያለአንዳች ማመንታት ይጋፈጣሉ፡፡

ይህ የኢትዮጵያዊያን ስብእና በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በተግባር የተንፀባረቀ ሐቅ ነው፡፡ አያሌ ጥቁር የዓለም ህዝቦች ጨካኙን የቀኝ አገዛዝ ስርዓት ለመቀበል ሲፈቅዱ ኢትዮጵያዊያን ግን ተጋፈጡት፡፡ ያኔ ጥንታዊያን አባቶቻችንና እናቶቻችን ቀኝ ግዛትን ለመመከት ሲነሱ ይህ ነው የሚባል የውጊያ ክህሎት ኖሯቸው አይደለም፡፡ የቀኝ ገዢዎቹን የኃይል ወረራ ለመመከት ቀርቶ አንዲት ስንዝር የሚያስኬድ የጦር መሳሪያም ታጥቀው አልነበረም፡፡ ሆኖም ግን ማንም ዘንድ ያልነበረ አንድ ኃይል በውስጣቸው ታጥቀው ነበር፡፡

በዘመናዊ ስልጠና የተጠናከረውንና ዘመናዊ በሆኑ የጦር መሳሪያ ብረቶች የተደራጀውን የቀኝ ገዢውን ወራሪ ኃይል አሸንፈው ከምድራቸውና አፈራቸው  ያባረሩት በእውነት፣ በፍትህና በፍቅር የተሞላውን ውስጣዊ ስብእናቸውን በመጠቀም ነው፡፡ ይህ ነው ጦርና ጎራዴያቸውን እሳት የሚተፋ የጦር መሳሪያ እንዲሆን ያበቃው፤ ከወራሪው የአየር ኃይል ያለማቋረጥ ይዘንብ የነበረውን ጥይት መመከት ያስቻላቸው፡፡

በወቅቱ በዚህ የኢትዮጵያዊያን ጀግንነት በእጅጉ ተገርሟል፤ ሰልጥነናል የሚሉትንም ቀኝ ገዢዎች አስደንግጧል፡፡ ይህ ጀግንነት አሁንም ድረስ በዓለም ታሪክ ውስጥ እንደተወደሰ ነው፤ በየዘመኑ የሚፈራረቀው የኢትዮጵያ ትውልድንም እንዳኮራ ነው፡፡

ይህ ህዝብ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የቅርብ ጊዜ ታሪክም አለው፡፡ ኤርትራን የሚያስተዳድረው ሻእቢያ ጦርነት ለኩሶ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ ይህ ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያን በኃይል በማንበርከክ

ጥቅሙን ለማስጠቀብ ለጫረው የድንበር ወረራ ይህ ህዝብ የሰጠው ምላሽም ህዝቡ ለእውነትና ፍትህ የቆመ መሆኑን በግልፅ ያረጋገጠ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያዊያንን አስተዋይነት ለመግለፅ የሚያግዙ ሌሎች አገራዊ ክስተቶችም ይኖራሉ፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትራችን ህልፈተ ህይወት ጋር በተያያዘ የተፈጠረው የሐዘንና የቁጭት ስሜትም የኢትዮጵያዊያንን ልዩ ስብእና የሚያንፀባርቅ ሌላ የታሪክ ክስተት አድርጌ እመለከተዋለሁ፡፡ ይህ ስሜት የዚህች ጥንታዊት አገር ህዝቦች ምን ያህል አስተዋይ እንደሆኑ በጉልህ ይመሰክራል፡፡

የመለስ ዜናዊን ህልፈተ ህይወት ተከትሎ ኢትዮጵያዊያን መንፈስ ውስጥ የተፈጠረው የሐዘንና የቁጭት ስሜት ኃያል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች መለስን በሞት በመነጠቃቸው የተሰማቸውን ሐዘን ቃላት አይገልፁትም፤ ተነግሮ የሚያልቅም አይደለም፤ ጥልቅና በእውነተኛ ከተሰበረ ልብ የመነጨና መሪር ነው፡፡

መለስ ማረፋቸው ከተነገረባት እለት አንስቶ የሚሰማውም ሆነ የሚታየው ለቅሶ ነው፤ ህዝቡ የማንንም ጥሪ አልጠበቀም፡፡ በራሱ ተነሳስቶ ድንኳን በማቆም አልቅሷል፤ በተለያየ መልኩም ሐዘኑን በመግለፅ ላይ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያዊያኑ ይህንን መሪር ሐዘናቸውን የሚገልፁበት መንገድ ያጠራቸው ይመስላል፡፡ አደባባይ ወጥቶ ያለቅሳል፤ መለስ መኖሪያ ቤት ድረስ በመትመ ስሜቱን ይገልፃል፤ እቅፍ አበባ በማዘጋጀት፣ የተለያዩ ፎቶግራፎቹን በመግዛትና ስንኝ በማቋጥር ወዘተ. ውስጣዊ ፍቅሩንና ሐዘኑን ለመግለፅ ቢሞክርም እርካታ አይታይበትም፤ በአጠቃላይ ክስተቱ የእግር እሳት የሆነበት ይመስላል፡፡

ከሐዘኑ ጎን ለጎን ኃያል የሆነ ቁጭትም ውስጡን ያንገበግበዋል፡፡ መለስ ለዚህች ጥንታዊት ምድር ምን ማለት እንደነበሩ ማሰብ ይታክተዋል፡፡ ይህ ሕዝብ የሆነውንና የሚሆነውን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡ በታሪኩ ህይወቱን ሙሉ ለህዝብ ልእልና የቆመ አዋቂ መሪውን ማጣቱ የማይታመን ሆኖበታል፡፡ የተረጋጋ የግል ህይወትን ሳያጣጥሙ መለስ በማለፋቸው ህዝቡ ተቆጭቷል፡፡ የመለስ ውለታ ሊከፈል የማይችል ከባድ ነው በሚል ስሜትም ከፍተኛ ባለእዳነት ተሰምቷቸዋል፡፡

መለስ የሚሿትን ኢትዮጵያ በሰርክ ህሊናቸው ሲያልሙ ደግሞ የቁጭቱ ኃያልነት እየበረታ ሲያንገበግባቸው ይስተዋላሉ፡፡ "ምነው እርሱ ቀርቶ ሞት እኔን በወሰደኝ!" የሚለው ንግግር ሰሞኑን ከተደመጡት የሐዘን ስሜቶች የሚበዛው ነው፡፡

የሆነው ሆኖ መለስ ወደማይቀረው ዘልአለማዊ ዓለም ሄደዋል፡፡ ለሚወዱት ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ግን አንድ ህያው የሆነ ውርስ ትተዋል፡፡ ኢትዮጵያዊያኑ በሐዘንና ቁጭት ቢቃጠሉም ይህን ውርስ የግላቸው በማድረግ ከዘመን ዘመን ለማሸጋገር ቃል ኪዳንም በመግባት ላይ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም ሳያጣ የድሃዎች ሁሉ ድሃ ህዝብ ሆኖ ብዙ መቶ ዓመታትን ኖሯል፡፡ በእኔ እምነት ይህ ህዝብ ለሚያሳፍር ድህነት የተዳረገው አገሩንና ህዝቡን የሚወድ እንደዚሁም ለሕዝቦች መብት፣ ሰላም፣ ፍትህና ልማት መረጋገጥ ራእይ ያለው መሪ በማጣቷ ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን ከአያሌ ዘመናት የሰቆቃ ህይወት በኋላ ኢትዮጵያዊያ እውነተኛ የአገርና የወገን ፍቅርን የተሞሉ፤ ታላቅ የፍትህና ልማት ራእይን ያነገቡ  የአገር ተቆርቋሪዎችን አፈራች፡፡ ይህንን ስብእና ከተላበሱት መካከል እነመለስ ግንባር ቀደሞቹ ናቸው፡፡ መለስና የትግል ጓደኞቻቸው በኢትዮጵያ ስር የሰደደ ድህነት፣ ሰላም እጦትና ፍትህ መጓደል ከምራቸው ይጨነቁ ስለነበር እነዚህን ሁኔታዎች ለመለወጥ ትግል ጀመሩ፡፡ ህይወታቸውን መስዋእት ሊያደርግ በሚችለው በዚህ ትግል ውስጥ ሆነውም የወጣትነት እድሜያቸውን ቤዛ አደረጉ፡፡

እነመለስ ትግሉን የጀመሩት ወታደራዊ ስልጠና ወስደውና በጦር መሳሪያ ተደራጅተው አልነበረም፡፡ ለፍትህና እውነት ለመሞት የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ ህዝብ ቁርጠኝነት በመያዝ እንጂ፡፡

ይህ በእነመለስ አመራር የተከፈለው መስዋእትነትም በወርቃማ ድል ተጠናቀቀ፤ መለስና ሌሎች የኢትዮጵያ የቁርጥ ልጆችም በአገሪቱ የህዝቦች ነፃነትና  እኩልነት የተረጋገጠበት ስርዓት እውን እንዲሆን ግንባር ቀደም ምክንያት ለመሆን በቁ፡፡

አዲሱ ስርዓት አዲስ አገርና በአዲስ መንፈፅ የታነፀ ህዝብን ለመገንባት መሰረት ጣለ፡፡ ለዘመናት እየተፈራረቁ አገሪቱን ያስተዳደሩት መሪዎች ከልክ ያለፈ ጭቆና ስሜቱን ሰብሮት የኖረውን ህዝብ ስሜት ጠግኗል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ መለስ በጥልቅ እውቀታቸውና የአመራር ብቃታቸው የተጫወቱት ሚና የላቀ ነው፡፡ የመለስ አመራር ኢትዮጵያዊያን በየደረሱበት የሚያፍሩበትን ድህነት መዋጋት ዋነኛ ግቡ ነበር፡፡ ይህንን ከዘመን ዘመን እየተከተለ አልለቅ ያለንን ርሃብና ችግር ለመዋጋት የተካሄደው ትግል በብዙ ውጣ ውረዶች የተሞላ እንደነበር የነበርን የምናስታወሰው ነው፡፡

በወቅቱ መለስና የሚመሩት መንግስት ካለፉት ስርዓቶች የተረከበው ምንም ኃብት አልነበረውም፡፡ መንግስታዊ ተግባራቱን በወጉ ለማከናወን የሚያስችለው ይህ ነው የሚባል ገንዘብ እንኳ እጁ ላይ አልነበረም፡፡ እንዲያም ሆኖ የእነመለስ መንግስታዊ አመራር በሳልነት የተዘረጋው የፖለቲካ ስርዓት ህዝባዊነትን አጎናፅፎት ስለነበር የተጋረጡትን ችግሮች ሁሉ በመጋፈጥ ማለፍ ተቻለ፡፡

የአገሪቱን አንገብጋቢ ችግሮች ቀድሞ የተገነዘበው መንግስታዊው አስተዳደር የተለያዩ የልማት እርምጃዎችን ደረጃ በደረጃ ወሰደ፡፡ በቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ የአርሶ አደሩን የስቃይ ህይወት መግታት ነበር፡፡ ካለፉት 20 ዓመታት በፊት አርሶ አደሩ ምርታማ አልነበረም፡፡ ዝናብ እየጠበቀ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር የሚያመርተው፡፡

በዚህም እራሱን እንኳ በቅጡ መመገብ ተስኖት ከእጅ ወደአፍ የሆነ ህይወትን ለዘመናት ኖሯል፤ ከዚህም አልፎ በድርቅና ርሃብ ሳቢያ በየጊዜው የብዙዎች ህይወት እየተቀጠፈ ዘመናት ነጉደዋል፡፡ የአዲሱ መንግስት የልማት እቅድ ቁልፍ ትኩረትም  ይህንን የአገሪቱ አርሶ አደር ህይወትን መለወጥ ነበር፡፡

በዚህ ረገድ የተወሰዱት የእድገት እርምጃዎች የአርሶአደሩን ህይወት በእጅጉ ለውጠውታል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የመለስ ሚና የላቀ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት አርሶ አደሩ ዝናብ ከመጠበቅ ባለፈ ሌሎች አዋጭ ስልቶችን ማሰብ ጀምሯል፡፡ ዛሬ አርሶ አደሩ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በማምረት አብዛኛውን ጊዜውን ተኝቶ አያሳልፍም፡፡

በእነመለስ በሳል አመራር በተቀየሰው የግብርና ልማት ስትራቴጂ አማካኝነት ባገኛቸው ልዩ ልዩ ድጋፎችና እውቀቶች እየተጠቀመ ዓመቱን ሙሉ ማምረት ይዟል፡፡ ከዚህ በፊት ለእለት ጉርሱ ብቻ ይጨነቅ የነበረው የአገራችን አርሶ አደር ዛሬ ምርቶቹን ለገበያ በማቅረብ ኃብት ለማካበት ታድሏል፡፡ ሚሊየነር ሆነው የስራ አድማሳቸውን በማስፋፋት ላይ የሚገኙትም አያሌዎች ናቸው፡፡

ይህ የእነመለስ ራእይ የሞላበት አመራር የአርሶ አደሩን ህይወት ከመቀየር ባለፈ አገሪቱ በምግብ ራሷን የምትችልበትን ተስፋ ሰጪ መንገድንም አጎናፅፏል፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች በርሃብ ህይወታቸው አያልፍም፡፡ በአገሪቱ ጥቂት አካባቢዎች የሚፈጠር የተፈጥሮ አደጋን ተከትሎ ለሚከሰት የምግብ እጥረት አገሪቱ በራሷ አቅም የምግብ እህል በማቅረብ ምላሽ መስጠት የምትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡

ይህ በመለስ ግንባር ቀደም መሪነት የፈለቀው ራእይ አርሶ አደሩን ከዘመናት እንቅልፍ ያላቀቀ ታላቅ ውጤት ነው፡፡ ራእዩ አርሶ አደሩ የያዘው መሬት ምንኛ አንጡራ ኃብት መሆኑን እንዲገነዘብ በማድረግ መነቃቃትን ፈጥሯል፡፡

የግብርናው ዘርፍ ውጤታማነት የሳባቸው በርካታ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችም ኢትዮጵያ ውስጥ በሰፋፊ የእርሻ ልማቶች እንዲሳተፉ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡ ይህ ዘርፍ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች የስራ እድል የፈጠረ ከመሆኑም በላይ የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ አቅም በማጎልበት ረገድ የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡ የአገሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረትም በእጅጉ

ያግዛል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትጠራበት የኖረውን ርሃብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መግታት የሚቻልበት ወቅት መቃረቡን ያሳያል፡፡

የድህነት መለኪያ የሚባሉትን የትምህርት፣ የጤና አገልግሎትና መሰል መሰረተ ልማቶች ላይ ስር ነቀል ለውጥ ማምጣት የተቻለውም በእነመለስ ያላሰለሰና በሳል አመራር አማካኝነት ነው፡፡ ዛሬ ሚሊዮኖች በየቄዬአቸው ትምህርታቸውን መከታተል የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ በጤና አገልግሎት እጦት ምክንያት ለሞት የሚዳረጉት የአገሪቱ ገጠር ቀበሌ ህዝቦች ቁጥር ዛሬ በእጅጉ ቀንሷል፡፡

መለስ ላለፉት 20 ዓመታት የመሩት መንግስት አገሪቱ ለምትገነባው ኢኮኖሚያዊ ልማት ወሳኝ የሆኑ ሌሎች አመርቂ ተግባራትንም አከናውኗል፡፡ አገሪቱ ባለፉት ዓመታት የገነባቻቸው መንገዶች የአገሪቱን የልማት አጋሮች ጭምር ያስደመመ ውጤታማ ተግባር ነው፡፡ ኢትዮጵያ ያለንምም ጥቅም አቅፋው የኖረችውን የውሃ ሃብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ተስፋ ሰጪ ራእይ የመነጨውም ባለፉት 20 ዓመታት የመለስ አመራር ዘመን ነው፡፡

የእነመለስ የዘውትር ህልም በአንድ ወቅት የዓለም ኃያል የነበረችውን ኩሩ አገር ለነበረችበት ታላቅነት ማብቃት ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት የሚያስችል መሰረት ተጥሏል፡፡ የእስካሁኖቹ ራእዮቹ ውጤትም ታላቅ ሕዝባዊ መነሳሳትንና መነቃቃትን በመፍጠራቸው የተጀመረው የእድገት ጎዳና እንዲቀጥል ዋነኛ ሞተር ሆኖ ይቀጥላል፡፡

ኢትዮጵያዊያን የሆነውንም ሆነ የሚሆነውን ሁሉ ጠንቅቀው የሚያጤኑ አርቆ አሳቢዎች ናቸው፡፡ ያለፉት 20 ዓመታት የመለስ አመራር በመላው አገር ወዳድ ሕዝብ ውስጥ ድህነትን ማሸነፍ የሚያስችል ወኔን ፈጥሯል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እድገትንና የአገር ኩራትን ሊያጎናፅፍ የሚችል ሰፊ ኃይል መኖሩንም አመላክቷል፡፡ ይህም እውን ይሆን ዘንድ ዘውትር የሚንን ዜጋንና የሚንተገተግ ውስጣዊ የእልህ መንፈስን ዘርቷል፡፡ ለዚህም ነው በመለስ ህልፈተ ህይወት በማዘን የሚደንቅ መገንተኝነታቸውን በማሳየት ላይ የሚገኙት፡፡

ለዚህች አዲስ የኢትዮጵያ ታሪክ ምክንያት የሆነው ራእይ መሪ መለስ ለዚህ ህዝብ እውነትም ታላቅ ባለውለታ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያዊያን ውለታን መክፈል አንዱ ባህላቸው ነው፡፡ መለስ ሌት ተቀን የደከሙለትን ራእይ ከግብ በማድረስ ውለታውን መክፈል እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡ በተለያየ መንገድ እየገለፁት ባለው የሐዘን መግለጫቸውም ይህንኑ በማረጋገጥ ቃል በመግባት ላይ ናቸው፡፡